# ታላቁ የወያኔ/ኢሕአዴግ

# የምርጫ ሴራ እና የተቃዋሚው ንፍዘት!

ወያኔ/ኢሕአዴግ ዲራማቲክ (ትዕይንተ ሁነታዊ) በሆነ መንገድ የምርጫ ዝግጅቱን አጧጡፎ ተያይዞታል፡፡ ተቃዋሚው ደግሞ ፈዞና ደንዝዞ የወያኔ/ኢሕአዴግን እጅግ አታላይና ዲራማቲክ (ትዕይንተ ሁነታዊ) የሆነ የምርጫ ዝግጅት በከፍተኛ ተመስጦና ደስታ በታዳማነትና አሚሚቂነት ጭምር ከመመልከት ውጭ አገዛዙ እያደረገው ያለው ነገር የምርጫ ዝግጅት መሆኑን እንኳ መረዳት አልቻሉም!

አገዛዙ የሚፈልገው እንዲህ እንዳንቀላፉና እንደፈዘዙ የቤት ሥራቸውን ሳይሠሩ ምርጫው ላይ ሊያደርሳቸውና ባልተዘጋጁበት ሁኔታ ተወዳድረው "አሸነፍኩ!" ሊል ነው፡፡ እነ እንቅልፎ ግን ሐሳባቸውና እየጠበቁ ያሉት አገዛዙ ምርጫውን አራዝሞላቸው በቂ ዝግጅት አድርገው "ነጻ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ ያደርግልናል እኛም አሸናፊ እንሆናለን!" ብለው ነው እየጠበቁ ያሉት፡፡

አገዛዙ ጥቅሙን ማስከበርና ማሸነፍ የሚፈልግ እንደመሆኑ ምርጫው ሳይራዘም ተቃዋሚው እንደተዝረከረከ በዝግጅት ማነስ እንዲወድቁ (ፌይል እንዲያደርጉ) እንደሚፈልግ እንኳ የሚጠረጥርና ያለችው አጭር ጊዜ በፈቀደችው መጠን ለመዘጋጀት የሚያስብና የሚያሳስብ አንድ ነፍስ ያለው ሰው እንኳ እንዳላቸው አልታየም፡፡

ሁሉም አገዛዙ የሚያደርገውን በመጠበቅ ዓይን ዓይን ዕያዩ ተቀምጠዋል እንጅ እንደ ባለድርሻ ወይም ጉዳዩ በቀጥታ እንደሚመለከተው አካል የጊዜውን አጭርነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነጻ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ ወይም ዝግጅት እንዲደረግ ለማድረግ አገዛዙን ሲጎተጉቱ ሲያሳስቡና ሲያስገድዱ አይታዩም፡፡

አገዛዙ እያሰበ ያለው ቀጣዩ ምርጫ ከዚህ ቀደም ከፍተኛ ማጭበርበርና ማወናበድ እየፈጸመ ወያኔ/ኢሕአዴግን አሸናፊ ሲያደርግ በቆየው የምርጫ ቦርድ (ባለአደራ) እንዲከናወን ነው፡፡ አገዛዙ ተቃዋሚዎች ጫና ከፈጠሩ ከላይ ያሉትን ሁለት ሦስት ሰዎች ወያኔነታቸው በማይታወቅ ሰዎች በመተካት ለውጥ ያደረገ በመምሰል ምርጫ ተብየውን ቅርጫ ለመፈጸም ተዘጋጅቷል፡፡ የምርጫ ቦርድ (ባለ አደራ) ማለት ግን ከላይ ያሉት ሦስት አራት ሰዎች ብቻ ማለት አይደለም፡፡ ይህ የምርጫ አስፈጻሚ ባለአደራ በመላ ሀገሪቱ አምስት መቶ ሽህ አባላት ወይም ሠራተኞች ነው ያሉት፡፡ሥራው የሚሠራው በእነኝህ ነው፡፡

እነኝህ ደግሞ በሙሉ የወያኔ ተቀጣሪዎች ወይም ታማኞች ናቸው፡፡ ተቃዋሚው "እነኝህ ካልተለወጡ አንወዳደርም!" የሚል የጸና አቋም ቢይዙና ወያኔ እሽ አይልም እንጅ ለመለወጥ ቢስማማ እንኳ ያለው ጊዜ ተተኪ ነጻ ሰዎችን አሠልጥኖ ለመተካትና ነጻ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ ለማኪያሔድ የሚበቃ አይደለም፡፡

ወያኔ ደግሞ ተቃዋሚው በቂ ዝግጅት ሳያደርግ ተንደፋድፎ ወደምርጫ እንዲገባና በዝግጅት ማነስ ብቁ ተፎካካሪ እንዳይሆንና እንዲሸነፍ ስለሚፈልግ የምርጫውን ጊዜ ፈጽሞ ማራዘም አይፈልግም፡፡ ወያኔ ወይም ዐቢይ ምርጫው እንደማይራዘም ከወዲሁ ለተቃዋሚዎች እንቅጩን መናገር የማይፈልግበትም ምክንያት ተቃዋሚው "ምርጫው

ይራዘማል!" በሚል ተስፋ እንዲዘናጋ በማድረግ ያለዝግጅት ምርጫ ላይ እንዲቀርቡ ለማድረግ ስለሚፈልጉ ወይም ስላሴሩ ነው፡፡

ሌላው እንኳ ቀርቶ ከውጭ የገባው ተቃዋሚ በመላ ሀገሪቱ በነጻነት ተንቀሳቅሶ ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኝና አቀባበል እንዳይደረግለት ሴራ እያሴሩ እስከማሰናከል የደረሱትም ለዚህ ነው፡፡ ለምሳሌ በአፋርና በጋምቤላ ሕዝብ ላይ ያተኮሩ ተቃዋሚዎች ጨርሶ ከሕዝባቸው ጋር እንኳ እንዲገናኙና አቀባበል እንዲደረግላቸው አልተፈቀደላቸውም፡፡ ግ7ም አገዛዙ የአማራ ክልል ብሎ ከሚጠራውና ከአዲስ አበባ በስተቀር በሌሎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ግን የተለያዩ ምክንያቶች እየተጠቀሱ ከሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ ተደርጓል፡፡ አገዛዙ ኦነግንና ግ7ን ማጋጨት የፈለገውና የሞከረውም በኦነግ እያሳበበ ግ7 ኦሮሚያ በሚለው ክልል እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ እንዲመቸው ነበር ተሳክቶለታልም፡፡ አገዛዙ የሚያወዛግቡ ነገሮችን የሚፈጥረውና አለመረጋጋት እንዲኖር የሚያደርገው ሆን ብሎ ነው፡፡ ይሄ ተግባሩም እስከ ምርጫ ድረስ ይቀጥላል፡፡

የዚህ ጉዳይ ዓላማም "የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል!" እንዲሉ ለስርቆት ለማወናበድና የፈለገውን ለማሰር ለማዋከብ እንዲመቸው፣ ሕዝቡንና ተቃዋሚውን ሥራ ለማስፈታት ጊዜውን በከንቱ ለማባከን፣ መግባባትና መረጋጋት እንዳይፈጠርና በክፍተቱ ተጠቃሚ ለመሆን ነው፡፡ በግ7 አቀባበል ምክንያት በአዲስ አበባ ላይ የተከሰተው ሞቅ ያለ መነቃቃት እንኳ አሳስቧቸው ሕዝቡን ወደነበረበት ድብርቱ ለመመለስ በማሰብ ነው አገዛዙ ሕገወጥ የሆነና በሕግ ያልተደነገገ ምክንያት በመጥቀስ በሕገወጥ መንገድ ወጣቱን "ፈቃድ ባልተሰጠው ሰልፍ ተሳትፋቹሃል፣ ጫት ቤት ሺሻ ቤት ተገኝታቹሃል!" እያለ በጅምላ እያፈሰ ከሦስት ሽህ በላይ ወጣቶችን በግፍ በማሰር እርምጃ የወሰደው ለዚህ ነው፡፡

ተቃዋሚዎቹ ግን ምን እየተካሔደ እንዳለ ፈጽሞ የገባቸው አልመሰለኝም፡፡ "የለውጥ እንቅፋቶች ናቸው እንዲህ እያደረጉብን ያሉት!" እያሉ እራሳቸውን በማጃጃል ላይ ይገኛሉ፡፡ ጥሩ እራስን የማጃጃያ ምክንያት አግኝተሃል ምድረ ጅል፡፡ አገዛዙ ገና ብዙ "የለውጥ እንቅፋቶች ናቸው እንዲህ እያደረጉብን ያሉት!" እያልክ የምትጃጃልበትን የግፍና ደም አፋሳሽ ጨዋታዎችን አዘጋጅቶልሃል ያኔም "የለውጥ እንቅፋቶች ናቸው እንዲህ እያደረጉብን ያሉት!" እያልክ እራስህን አጃጅልለት እሺ???

የሕግ አካላትና የመንግሥት ተቋማት በሙሉ "የለውጥ አደናቃፊዎች!" በምትላቸው የተሞላ መሆኑ ከገባህ የለውጥ ኃይል የምትላቸው በጣት የሚቆጠሩ የወያኔ ድርሰት መሪ ተዋንያን ምንም ሊፈጥሩ እንደማይችሉ ተረድተህ መፍትሔው ስርነቀል ለውጥ መሆኑን መገንዘብ ከተሳነህ እያንዳንድህ እስክትበላ ድረስ "ዓይንህን ጨፍን ላሞኝህ?" ጨዋታህን ከወያኔ ጋር መጫወትህን ቀጥል!

አገዛዙ ሁለት ዓይነት ገጽታ ማለትም የለውጥ ኃይልና የለውጥ አደናቃፊ የሚል ገጽታ የያዘበት ምክንያት እንዲህ ዓይነት ጨዋታ በመጫዎት ጥቅሙን ለማስከበር፣ ቁማር ለመቆመር እንዲመቸው እንደሆነ ገና ከጅምሩ ነግሬያቹህ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ ተቃዋሚዎቹ በእነሱ ምክንያት በሕገወጥ መንገድና በሕገወጥ ምክንያቶች እየታፈሰ ስለታሰረው ወጣት እንኳ ሊጮኹና ጫና ፈጥረው ሊያስፈቱ አልቻሉም፡፡ ስለ እነሱ ሲል ለዚህ ግፍ ስለተዳረገው ወጣት ሳይጮኹና ጥብቅና ሳይቆሙ ነገ ማን ይደግፈናል ብለው እንደሚጠብቁ በእውነቱ አላውቅም፡፡ አንድ እንኳ ማሰብ የሚችል ሰው የላቸውም፡፡

እውነቱን ንገረን ካላቹህኝ በአገዛዙ ሴራ፣ ሽፍጥና አሻጥር ተጃጅሎና ተሸውዶ የሚጎተት እንጅ የፖለቲካ ስሌት የሚችልና ነገሮችን ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እያገናዘበ አባዝቶና አካፍሎ፣ ደምሮና ቀንሶ ጥቅሙን ለማስጠበቅና ጥቅም ለማግኘት እየቀደመ የሚያስብ አንድ እንኳ የተቃዋሚ መሪ መኖሩን እኔ አላውቅም፡፡

በአንጻሩ ግን ወያኔ እንደምታዩት ያለ እረፍት ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡ የብአዴንና የኦሕዴድ ስም አርማና ርዕዮተዓለም የመቀየር እንቅስቃሴ ያደረጉት የምርጫ ዝግጅት አካል ነው፡፡ እንደ አገዛዙ ሐሳብ በቀጣዩ ምርጫ ኢሕአዴግ

የሚለውን ቀፋፊ ስም፣ አርማ፣ አቢዮታዊ ዲሞክራሲ የሚለውን የወያኔን ግፍ የሚያስታውስ ርዕዮተ ዓለምና እነኛን ቀፋፊ መሪዎችን ወይም እጅግ በሕዝብ የሚጠሉ አመራሮቻቸውን ይዘው መቅረብ አልፈለጉም፡፡ አሁን አሰናበትን አባረርን ምንትስ ብለው ቢሸኟቸውም ከምርጫው በኋላ ግን ይመልሷቸዋል፡፡ ስም አርማንና ርዕዮተዓለምን በተመለከተ ብአዴንና ኦሕዴድ የየራሳቸውን ቀይረዋል፡፡ ደኢሕዴን ከ11ኛው የኢሕአዴግ ጉባኤ በኋላ እንደሚቀይር አስታውቋል፡፡ በመጨረሻም የጋራቸው የሆነውን ስማቸውን፣ አርማቸውንና ርዕዮተዓለማቸውን ይቀይሩትና ለምርጫ ይቀርባሉ፡፡

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲሰማው ልቡን የሚያጥወለውለውን ኢሕአዴግ የሚል ስም፣ አርማና አቢዮታዊ ዲሞክራሲን ለውጠው ወይም ጥለው በአዲስ ስምና ርዕዮተዓለም ምርጫ ላይ በመቅረብ ነጻ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ በሚመስል ምርጫ አጭበርብረው በማለፍ ኢሕአዴጋዊ ማንነታቸውን በመቀየራቸውና በመለወጣቸው፣ ሕዝብ የሚጠላቸውን ባለሥልጣናት በመሸኘታቸው በሕዝብ ተቀባይነትን አግኝተው እንዳሸነፉ ለማወጅ በሚገባ ተዘጋጅተዋል፡፡

ይሄንን ሒደት እርስ በእርስ የተጋጩ፣ ያልተስማሙ በመምሰል ስም፣ አርማና ርዕዮተዓለም በተናጠል እየቀየሩ ሰዎቻቸውንም እየቀየሩ የመምጣት ሥራ እየሠሩ ያሉት ተቃዋሚው እንዳይነቃባቸውና ተቃዋሚው ድራማውን (ትውንተ ሁነቱን) አፉን ከፍቶ በመዘናጋት እየተመለከተ ጊዜውን በማባከን ሳያስበው ምርጫ ላይ እንዲደርስና ሳይዘጋጅ ተወዳድሮ እንዲሸነፍ ለማድረግ ነው፡፡

ወያኔ በምታዩት መልኩ እንዲህ ዓይነት ድራማ (ትውንተ ሁነት) እየተጫወተ፣ እያሴረ፣ እየሸፈጠና እያሻጠረ ማድረግ ያለበትን ሁሉ አድርጎ ሥልጣኑን እንደያዘ ይቀጥላል እንጅ የፈለገ ነገር ቢፈጠር፣ በምንም ተአምር ቢሆን ነጻ ፍትሐዊና ተአማኒ ምርጫ አድርጎ ሥልጣን ያስረክባል ብላቹህ እንዳትጠብቁ!!!

ይሄንን እንኳን በእውናቹህ በሕልማቹህ እንኳ አታዩትም፡፡ ወያኔ ሊወገድ የሚችለው በአንድና አንድ መንገድ ብቻ ነው፡፡ እሱም ከፊት ለፊቱ ያገኘውን የወያኔን እና የብረት ምርኩዞቹን እኅት ድርጅት ተብየዎችን አባላትና አመራሮችን ቀረጣጥፎ መብላት በሚችል መሬት አንቀጥቅጥና የጨከነ ሕዝባዊ ዐመፅ ብቻና ብቻ!!!...

እያንዳንድህ አመንክም አላመንክ፣ ወደድክም ጠላህ እውነቱ ይሄ ነው!!! ከዚህ በመለስ ባሉ አማራጮች በሙሉ ወያኔ ይወገዳል፣ የጠፋል ወይም ይወድቃል ብለህ የቁም ቅዠትህን የምትቃዥ ካለህ ቃዥተህ ትቀራለህ እንጅ ቅዠትህ እውን የሚሆን እንዳይመስልህ!!! ምድረ ጅላጅል ቃዣታም ሁላ ወያኔን እንዲህ በዋዛ በቀላል ልትገላገይ??? መስሎሻላ iii ገና ገና ብዙ ይቀልድብሻል በነፍስ በሥጋሽ ይጫወትብሻል!!!

ኧረ እባካቹህ ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) የማትችሉና የማታውቁ ፖለቲካ ሠሪ የተቃዋሚ ድርጅቶች፣ አክቲቪስቶች (ስሉጣን)፣ ጋዜጠኞች፣ የመብት ተሟጋቾች፣ ጸሐፊዎች፣ ነጻ የብዙኃን መገናኛዎች በተለይም ኢሳት ወዘተረፈ.. እባካቹህን እባካቹህ አሁን እንኳ ንቁ???... ተጃጅላቹህ ሕዝብ ማጃጃላቹህን አቁሙ???... በቃ የቀን ቅዠታቹህ እዚህ ላይ ይብቃ!!! ቅዠታቹህን አምላኪ ሆናቹህ ነው እንጅ በየዕለቱ የሚያነቃ ነገር እኮ አልጠፋም ነበረ፡፡ በቅዠታቹህ ታውራቹህ "የለውጥ አደናቃፊዎች ናቸው እነ ዐቢይ አይደሉም!" እያልክ እራስህን እያጃጃልክ በየት በኩል ታስተውለዋለህ ታዲያ አንተ???

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com